# አስመሳይ ተቃዋሚዎች በስራቸው ሲጋለጡ

ከዳኛቸው በፈቃዱ

በተቃዋሚ ስም የሚንቀሳቀሱ አስመሳዮች ለምርጫ 97 ውጤት መነጠቅና ለወያኔ በሥልጣን መቆየት ከፍተኛ ሚና መጫዎታቸው በሰፊው የተጻፈ፣ የአደባባይ ምፅጢር ነውና ዝርዝር ውስጥ መግባት አልፈለግኩም። ይሁን እንጂ፤ ዛሬም ቢሆን አስመሳዮች ትግሉን ለማደናቀፍና ህዝቡን ለማደናገር የሚያደርጉትን ጥረት በአገር ውስጥም ሆነ ካገር ውጪ እንደቀጠሉ ናቸው። ምንም እንኳን፤ ዓላማቸው የታወቀ ቢሆንም በእያንዳንዱ ዕለት የተለያየ ማስመሰያ ይዘው ከመውጣቸው የተነሳ አንዳንድ እውነተኛና አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን ማደናገርና አንዳንዶቹን ለመሰሪ ዓላማቸው መሣሪያ ማድረግም ችለዋል። ደግነቱ እያንዳንዱ የማደነገሪያ ዕርምጃቸው አስመሳይነታቸውን እያጋለጠ በመሄዱ ብቻቸውን ማጨብጨብ ከጀመሩ ቆይቷል። ዛሬ የማደናገሪያ ስልት አልቆባቸው ፣ የውሸት ኮሮጆአቸው ተመናምኖ፣ የከዱትና ሊያታልሉት የሚሞክሩት፣ ህዝብ ፤ ቀድሚቸው ሄዶ የኋሊት እየተመለከታቸውና እየታዘባቸው መሆኑን እንኳን ማየት ተስኗቸዋል።

በተጨማሪም ፤ አስመሳይ ተቃዋሚዎች ትናንት ምን ይሉ ነበር ? ዛሬስ ምን እያሉ ነው? የሚሉትን እንዲሁ ለማስታወስ ያህል፤ እስኪ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ልሞክር።
አንድነት ሃይሎችን፤ አክራሪዎች፣ ነፍጠኞች ወዘተ... ሲሉ ቆይተዋል። ዛሬም እንደቀጠሉ ናቸው። የትግል አንድነት ጥሪ አደርገናል ይሉና ፣ ከአንድነት ሃይሎች ጋር አብሮ መስራት አይቻልም፤ ምክንያቱም እነሱ ወያኔ/ኢሕአደግ ጠላት ነው ይላሉና። እኛ ግን ከወያኔ ጋር እንድ ላይ መስራት ይቻላል ብለን እናምናለን ብለው ይሰብኩናል። ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና አሠራር መሠረት ለሆነው ለብዙሃን ድምፅ አንገዛም ብለው፣ ጉባኤ ረግጠው ይወጡና "እኛ ዴሞክራሲያውያን ነን ፣ ነገር ግን የብዙሃን ድምፅ የያዙት አምባገነን ናቸው" ሲሉ፤ የወያኔን ለህዝብ ድምፅ አልገዛ ማለትን በእጅ አዙር ሰደግፉ አያየናቸው እየሰማናቸውም ነው። ጉደኛ "ተቃዋሚዎች!" ወያኔስ ቢሆን ለብዙሃን ድምፅ አልገዛም አይደል ያለው። ለነገሩ ገብተን ከወያኔ ጋር አብረን እንሰራለን ሲሉ ማንነታቸውን ገልፀውልናልና፤ ብዙም የሚደንቀን መሆን የለበትም።

በበርካታ መረጃ የተደገፉ ዘገባዎች እንዳመለከቱት፤ ከ50ሺህ በላይ ኢትየጵያውያን በወያኔ እስር ቤት ታጉረው በሚገኙበት ወቅት፤ የአስመሳይ ተቃዋሚዎች ወኪልነን ባዮች ደግሞ፤ በአሜሪካ ኮንግሮስ ፊት በቀረቡበት ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ስንት የፖሊቲካ እስረኛ አለ ተብለው ሲጠየቁ "100 ይሆናል" ሲሉ ሰምተን፤ ምነው ብንላቸው መልስ በመስጠት ፈንታ ዙሪያ ጥምጥም ይጓዙና "በትግራይ ህዝብ ላይ በደል ፈጽመናልና ይቅርታ ይደረግልን" ብለው በተቃዋሚዎች ስም ይቅርታ ሲጠይቁም ሰማናቸው። በድንገት ተሳስተው ነው እንዳይባል አላስተባበሉም።

እዚህ ላይ መች አቆሙ ፣ "ወያኔን ጠላት አትበሉት" ብለው ለመስበክም ዳድቷቸው ነበር። ጭራሽ ይባስ ብሎ ፕሮፈሰራቸው "በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ዴሞክራሲን ያመጣው ወያኔ ነው" ሲል ፤ በአውስትራሊያ

ሜልበርን  ከተማ ሬዲዮ መናገሩን የሰማሁ ጊዜ ነው፡ ከእንግዲህ በዛ ያልኩት። እነዚህ ሃይሎች በፊተኛው ፋሽስታዊ መንግሥት ዘመን በኢትዮጵያ ህዝብ ደም ሲቀልዱ ቆይተው ፣ ያ ቡድን በወደቀበት ማግስት ደግሞ፣ ላሁኑ ጎሰኛ ፋሽስታዊ ቡድን "ታማኝ አገልጋይነታቸውን" ሲገልጹ፣  ቆይተው ፤ በሌላ በኩል የሰብአዊ መብት ጠበቆችና ዲሞክራቶች ነን ብለው ስያደናገሩ ፣ በምርጫ 97 የህዝብን ድምፅ በጉልበት የቀማውንና ከ200 በላይ ገሎ ፣ ከ50ሺህ በላይ በእስር ቤት ያጎረውን ወያኔን "ጠላት አትበሉት ፣ ዲሞክራሲ አመጣ ፣ ከወያኔ ጋር አብሮ መሥራት ይቻላል" ወዘተ እያሉ ፣ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የወያኔን ዓላማ ሲፈጽሙና ስያስፈጽሙ፣ በቃችሁ ልንላቸው ይገባል።

ከወያኔው መሪ ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር ተጣልተው ያፈነገጡ፤ ነገር ግን ከህዝብ ጎራ ግልፅ ሆነው መግባት የማይፈልጉ ወያኔዎችን ይዘው እየዞሩ፣ ወይንም የተናገሩትን እንደተማሪ ዲያቆን በየመንገዱ እየደጋገሙ "የኢትዮጵያ ጀግና" እያሉ ሲያስተዋውቋቸው ዝም ማለት የለብንም።  እነስዬ አብርሃንና ገብሩ አስራትን "በጀግንነትና በተቃዋሚነት" ህዝቡ እንዲቀበላቸው ሲሰብኩን ዞር በሉ ማለት አለብን።  መታወቅ ያለበት ዋናው ነጥብ ስዬ አብርሃ ጠቡ ከመለስ ጋር ነው እንጂ ከወያኔ ጋር አይደለም።  ለዚህም ማረጋገጫ ብዙ መደርደር ሲቻል ፣ ሁለት ነጥቦችን ማቅረብ በቂ ነው።

1ኛ.  አቶ ስዬ አብርሃ የወያኔን ምፅጢር በከፍተኛ ደረጃ እንደጠበቀ ነው።  ለምሳሌ፣ ሌላው ቀርቶ ወያኔ በግፍ ያሰራቸውን የት እንዳሉ ደብዛቸውን አጠፍቶ የያዛቸውን የፖሊቲካ እስረኞችን ጉዳይ ዛሬም ምፅጢር አድርጎ እንደያዘ ነው።  ስዬ አብርሃ ነው ከመለስ ዜናዊ ጋር ሆነው እነ ፀጋዬ ገ/መድህንና ሌሎችንም ያሰረው።  ትክክለኛ ተቃዋሚ ከሆነ የት እንዳሰሯቸው መናገርና ወያኔን ማጋለጥ አለበት እንጂ የወያኔን ምፅጢር እየጠበቀ ተቃዋሚ ነኝ ብሎ ልያታልለን ሲሞክር አቁም አንተ አሁንም ወያኔ ነህ ማለት አለብን።

2ኛ.  እስካሁን ባደረጋቸው ስብሰባዎችና ቃሌ-መጠይቆች ወያኔን ሲያወግዝ አልተሰማም።  ባንድነት መታገል በሚል እያደናገረ ለማለፍ ከመሞከር በስተቀር ወያኔን ሊያወግዝ ቀርቶ ቡድኑ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የፈጸማቸው ግፎች በጥያቄ መልክ እንኳን እንዳይነሱ ይደረጋል።  ምክንያቱም አቶ ስዬ ይቀየማልና።  አቶ ስዬ አገር አጥፊው ቡድን የተመሰረተበትን ዘረኛና ከፋፋይ ስርዓት ፤ ከስረ መሰረቱ ተነቅሎ እንዲወገድ አይፈልግም።

እንግዲህ እዚህ ላይ ነው ጨዋታው።  ጂሌዎቻቸው ሰሞኑን የተቃዉሞ ሥራ ሰራን ብለው በእስረኞች ፤ በዴሞክራሲና በተቃዋሚ ሃይሎች አንድነት ስም መጀመሪያና መጨረሻ የሌለውን "መግለጫ" ያሉትን በኢትዮሚዲያ ድረ-ገጽ አውጥተው አየሁ።  መግለጫው የወጣበት ከተማ ስም ሰለጠቀሱ ትክክለኛ ተቃዎሚ መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅ መንገዱ ቀጥተኛ ነበር።

"በግንቦት 7 መንፈስ ንቅናቄ" አስተባባሪነት አስቸኳይ ስብሰባ ማካሄዳቸውን ቢጠቅሱም፤ ስበሰባው መቼ እንደተካሄዶ አልተጠቀሰም። ወይም አስተባባሪ የተባለው ቡደን መግለጫ አላወጣም።  "ወቅታዊው የአገራችን

ሁኔታ ያሳሰበንና በምዕራብ አውስትራሊያ ነዋሪ የሆን ኢትዮጵያውያን መግለጫና ውስኔ" ብለው ነው ያወጡት። መግለጫው የሚጋጭና የማይጣጣም መልዕክት የያዘ በመሆኑ ማደናገሪያ መሆኑ ተረዳኝ። እውነትም ማደናገሪያ ፣ ከነስሙ የሚያደናግር ማደናገሪያ! እስኪ ምን ይላሉ እንመለከታቸው።

መግለጫው የሚለው ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር እጅግ ያሳዘነው መሆኑን ገልጸው ባስቸኳይ እንድትፈታ በጋራ እንታገል የሚል ጥሪ ያቀርባል። በሁለተኛው ነጥብ ላይ አቶ አበራ የማነአብና ፀጋዬ ገ/መድህን ለረዥም ጊዜ የተንገላቱት እንድፈቱ በጋራ እንታገል ይላል። ቡድኑ ስለእነዚህ ሁለት እስረኞች ጉዳይ ለማንሳት ይህን ያህል ጊዜ ለምን ወሰደበት? የብርቱካንን ብቻ ማንሳቱ አሳፍሮት ይሆን ስማቸውን ያስገባው ወይስ በትክክል ተቆርቁሪ ሆኖ ነው? ስለአንድነት ያደረገው ጥሪ በትክክል አንድነትን በተግባር ስለሚደግፍ ነው ወይስ ከወያኔ ጋር መሥራት እንችላለን የሚሉት ክፍሎች አካል ነው? የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎች በጭንቅላቴ ተመላለሱ። ለጥያቄዎቼ መልስ ለማግኘት ተንቀሳቀስኩ።

መልስ አገኘሁና ለወገን ማከፈል አለብኝ ብዬ ስለወሰንኩ ነው ለመጻፍ የተገደድኩት። ስለቡድኑ ምንነት ከሰራው ሥራ አኳያ አይቼ የማውቀውን በዝርዝር ልጥቀስ ። እንግዲህ ሥራው እንደሚከተለው ነው።

1. በአካባቢው ከሚንቀሳቀሰው ዴሞክራትና እንድነት ሃይሎች አፈንገጠው የወጡ በጣም ጥቂት ግለሰቦች ናቸው።

2. ከዴሞክራሲና አንድነት ሃይሎች ጋር መሥራት የማይፈልግና በመግለጫው ላይ አካሄድን ብለው በጠቀሱት ስብሰባም ቢሆን ከተገኙት 10 ሰዎች ግማሽ ከሚሆኑት ተሰብሳቢዎች "ከተቃዋሚ ሃይሎች ጋር አብሮ መሥራት" የሚል ሃሳብ ሲቀርብ አብረን እንሥራ የሚትሉ ከሆናችሁ እኛ ለብቻችን እንደራጃለን ሲሉ "አሥራችን በዝተን በሁለት እንከፈል?" በሚል ከሃዘንና ትዝብት ጋር በተቀላቀለ ስሜት የተገኙትም ያህል ሰዎች ቅረታቸውን ገልጸው ተለያዩ። ልብ በሉ! እንግዲህ እነዚህ ሰዎች ናቸው ተቃዋሚዎች አብረው መስራት አለባቸው የሚሉት።

3. ሌላው ተራና ዓይን ያወጣ ውሸት ደግሞ፤ ከመግላጫቸው ጋር አያይዘው ያወጡት የሠላማዊ ሠልፍ ፎቶግራፍ ነው። ፎቶግራፉ በ2005 በአካባቢው በሚንቀሳቀው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ መድረክ በሚባል ድርጅት አስተባበረነት በተዘጋጀው ሠላማዊ ሠልፍ የተወሰደ ፎቶግራፍ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል። ወያኔያዊ ቅጥፈት የመጣው እዚህ ላይ። ወያኔ "ተራራን ያንቀጠቀጠ ትውልድ" በሚል አርእስት ያስጻፈው መጽሐፍ ትዝ አለኝ።

4. ጥያቄያቸው የአዞ ዕንባ መሆኑን የሚያመላክቱ በርካታ መረጃዎች አሉ። በመጀመሪያ መግለጫቸው አፍቃሪ-ስዬ በሆነው ድረ-ገፅ በኢትዮሚዲያ መውጣቱ ሲሆን ፤ መግለጫቸውን እስካወጡበትና ከዚያም ወዲህ እነዚህ ግለሰቦች ስዬ አብርሃንና ገብሩ አሥራትን የሚያደንቁና እያደነቁ ያሉ ግለሰቦች ናቸው።

እነዚህ ለገዳይ የጅግንነት መዳሊያ ለሟች አበባ የሚያቀርቡ ተራ አስመሳዮች ናቸው። ፀጋዬ ገ/መድህንና አበራ የማነአብን ያሰረውን በአዲስ አበባ በርካታ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችንና ወጣቶችን በግፍ የጨፈጨፈው ቡድን ቀንደኛ መሪ የነበረውንና ዛሬም ቡድኑን ማውገዝ የማይፈልገውን ፤ አቶ ስዬ አብርሃን ጅግና እያሉ እያደነቁ፣ እነሱ እንዲፈቱ እንጠይቃለን ማለት፤ እንደነመለስ ገለው ማልቀስና ጥቁር ካርባት አስረው ለቀብር መሄድ ሆነብኝ። ጉደኛ ተቃዋሚ! አሁንስ ማስመሰልም አቃተው።

የግንቦት 7 ጉድ እንዴት በዝምታ ይታለፋል። የአርበኝነትን ምስክር ወረቀት በ500 ዶላር ለመቸብቸብ የተንቀሳቀሰውስ ምን ይባላል? ወይ ጉድ! አርበኝነት እንደዋዛ በ500 ዶላር የሚሸጥ ከሆነ ሰዎች ውድ ህይወታቸውን ለምን መስዋዕት ይከፍሉ ነበር? በብር እየገዙ እቤት ቁጭ ነው እንጂ። ይህ አርበኝነትን ዋጋ ለማሳጣትና ታጋይ እንዳይወጣ ለማድረግ የተቀነባበረ ብሔራዊ አሻጥር ነው። ወያኔም የኢትዮጵያዊነት መታወቂያ በ500 ዶላር ይሸጣል ፤ ግንቦት 7ም የአርበኝነት ምስክር ወረቀት በ500 ዶላር በሶፋ ላይ ቁጭ እንዳሉ ያቀርብልዎታል። ጉድ ነው ዘንድሮ! የወጭ ምንዛሪ አጥቶ የሚቸገረው ወያኔ የኢትዮጵያዊነት መታወቂያ ዋጋ ወደ 1000 ዶላር ከፍ ካደረገ ግንቦት 7ም የአርበኝነት ምስክር ወረቀት ዋጋ ከፍ ያደርጋል ማለት ነው? ምናልባት ግንቦት 7 የዉጭ ምንዛሪ ችግር ስለለበት ላይጨመር ይችላል። ይህን ዓይነት ከወያኔ ሥራ ጋር ተመሳሳይነት ያለውን አሰራር እንዴት ይዘው ወጡ? ፋክክር ነው? ወይስ ምንድነው? መቼም የሚፎካከሩ አይመስለኝም። አንድ ዓይነት ሥራ መሥራት ስላለባቸው ነው። መሪው ዶ/ር ብርሃኑ በወያኔ ኢኮኖሚ እንሸሽት ማድረግ እንዳላብን ይሰብክን ነበር። ቀጥሎም በምርጫ 97 ከዶ/ር በየነ ጋር በመሆን ብሔራዊ አድማ እንድከሽፍ አደረገ። ለውሌታው ወያኔ አስርኩት ብሎ መፈናፈኛ በለለበት በወያኔ እስር ቤት በ6 ወር ውስጥ 600 ገጽ መጽሐፍ እንድጽፍ እድል አገኘ። ብዙም ሳይቆይ “መታሰር የለለበት ጭንቅላት” ተብሎ በወያኔ ጋዜጣ ተጻፈለት። የአርበኝነት ስሜት ከገደለ ምን ይከፈለው ይሆን?